# የወያኔ ክንዶች እየዛሉ ነው!

March 15, 2017

**ተሻለ መንግሥቱ (teshalem1@gmail.com)**

“የውኃ ጠብታ – እያደር – ድንጋይ ይሰብራል” መባሉ አለብልኃት አይደለም፡፡ ሕወሓት ወደ ኢትዮጵያ ፖለቲካ ዘው ብሎ እንደገባ ውልቅ ብሎ መውጣት እንዳልቻለና እንደማይችልም አሁን አሁን ቁልጭ ብሎ እየታዬ ነው፡፡ ያገሬ እረኛ “ስወጣ እንደጦጣ ስወርድ ምንትሴ መጣ” ይላል፡፡ ሁሉ ነገር ሲጀምሩት ቀልድና ቧልት ይመስላል፡፡ ለተወሰነ ጊዜ ሁሉ ነገር አልጋ ባልጋ ሆኖ ሲታይ እስከወዲያኛው እንደዚሁ እንደሆነ የሚዘልቅ መስሎ ይታይና ራስን እስከማነሁለል ለሚያደርስ ዕብሪት ሊዳርግ ይችላል፡፡ አስተዋይ ግን ግልባጩንም አሰብ ያደርግና ጥንቃቄ ያደርጋል፡፡ ለዱባ ጥጋብ አይንበረከክም፡፡

ቆዳ ለባሽና ለዓለማዊ ሙብለጭለጭ ብዙም ደንታ ያልነበራቸው አንድ ባላገር ሀብታም ሽማግሌ ነበሩ፡፡ ብዙ የቀንድና የጋማ ከብት፣ ብዙ የጎተራና የጉድጓድ እህል ነበራቸው፡፡ በዱርም በቤትም በሚርመሰመሱ አሽከሮችና ወፍ ከሰማይ በሚለቅሙ አንጋቾች ታጅበው የተደላደለ ሕይወት ይመሩ ነበር፡፡ አንድ ቀን አንዱ ከብት ጠባቂ በደስታ እየተፍነከነከ ሲሮጥ ይመጣና “አብዬ! የምሥራች! ዛሬ ሌሊት ብቻ ከየበረቱ 50 ላሞች ወልደው አደሩ!” ይላቸዋል፡፡ እስከዚያን ጊዜ ድረስ ያን ያህል ጥገት በአንድ አዳር ታይቶ አይታወቅምና ሰውዬው በደስታ እንደሚፈነጥዙ አምኖ ነበር እረኛው እንዲያ ያለው – የዘንድሮን ሀብታም መስለውት፡፡ እርሳቸው ግን ተከዝ አሉና “አይይ… አዱኛን ‹ሂጂና ሌላሽን ብይ› በላት” ነው ያሉት፡፡ ጳውሎስ ኞኞም በሩሕ መጽሔት ብዙ ገንዘብ ወደኮሮጆው ሲገባለት ጊዜ “ለጤና ያድርገው እንጂ ዘንድሮስ ገንዘቡ ታፈሰ” ብሎ ቀልዶ ነበር አሉ – አልሆነለትም፡፡ “የፈሩት ይደርሳል፤ የጠሉት ይወርሳል” ይባል የለም?

ሕወሓት በለስ ቀንቶት ከ1983 ዓ.ም ወዲህ ኢትዮጵያን በብቸኝነት ተቆጣጥሮ ያሻውን ሲያደርግ ቆይቷል፤ አሁንም እንደዚያው ነው፡፡ ነገር ግን ነገሮች በከፍተኛ ፍጥነት እየተለዋወጡ የሚገኙበት ሁኔታ ላይ መድረሳችንን በተለይ ከየጉራንጉሩ አንዳንድ ወሬ የመስማት ዕድል ያለን ዜጎች እየተረዳን መጥተናል፡፡ መቼም አፍ አይሞትም ወያኔ “አለሁ” ይላል እንጂ ጌታውን ከሎሌው፣ አዛዡን ከታዛዡ መለየት የማንችልበት የጨረባ ተዝካር ዓይነት ሀገራዊ ትርዒት እያየን ነው፡፡ ወረዳም ግባ፣ ክፍለ ከተማም ግባ፣ ማዘጋጃም ግባ፣ ወደ ሚንስቴር መሥሪያ ቤቶችም ጎራ በል … ብቻ የትም ግባ ከሞላ ጎደል ሁሉም ሰው ውክቢያ ላይ ነው፡፡ ሁሉም ኃላፊና የመንግሥት ሠራተኛ በተቻለው የየድርሻውን ቦጭቆ ዘወር ለማለትና የራሱን ቢዝነስ ከፍቶ እንደጌቶቹ ለመንቀባረር ጥድፊያ ላይ ይገኛል፡፡ (ለትውስታ – ወያኔ አዲስ አበባ ጫፍ ካራአሎና ለገጣፎ ደርሳ መናገሻዋን በአራቱም አቅጣጫ ወጥራ በነበረችበት ግምቦት 18 እና 19/1983 አካባቢ ሚኒስትሮችን ጨምሮ ጥቂት የማይባሉ የደርግ ሹማምንት የጀመሩትን ቤት ለመጨረስ ማርካቶ ውስጥ ቆርቆሮና ምስማር ይገዙ ነበር አሉ፡፡)

ሕወሓት ከገጠመው ታሪካዊ የመበስበስና የሙብከት እንዲሁም ከዚህች ምድር የመሰናበት የመጨረሻ ዕጣ ፋንታውን ለማስቀረት ወይም ቢያንስ የዘረጋውን የጥቁር በጥቁር አፓርታይድ ሥርዓት ዕድሜ ለማራዘም የከረረ ትግል ከጀመረ አንድ አራት ዓመታትን አስቆጥሯል፡፡ በተለይ ቁንጮዎቹ ሁለቱ ታላላቅ የወያኔ አጋፋሪዎች ከሞቱ ከ2004ዓ.ም ክረምት ወዲህ ቡችሎቻቸው በቤተ መንግሥትና በቤተ አምልኮቱ ይይዙትንና ይጨብጡትን አጥተው እንዳበደ ውሻ ያገኙትን ሁሉ እየነከሱና በመርዛቸው ለክፊው እየገደሉ ይገኛሉ፡፡ ይህ ፍርጃ ሊያመልጡት ያልተቻለ ኢትዮጵያዊ የመርገምት ናዳ ነው፡፡ ለማንኛውም ከድቅድቅ ጨለማ በኋላ ፍንትው ያለች ፀሐይ እንደምትወጣ እናምናለንና ሁኔታዎች በዚህ መንገድ የማይቀጥሉበት ነፃነትንም የምናገኝበት ዘመን በቅርቡ ይብታል ብለን ተስፋ እናደርጋለን፡፡

እነዚህን ያበዱ ውሾች ለመታገል በተለይ በአሁኑ ወቅት ሕዝቡ የማያደርገው ትግል የለም፡፡ ጥቂቶቹን ብንመለከት፡-

በብዙ አካባቢዎች በተለይም በጎጃምና በጎንደር ወጣቱና ጎልማሣው ዱርቤቴ ብሎ በጎበዝ አለቃ እየተመራ የወያኔውን መንግሥት ተብዬ ቡድን ባመቸው ጊዜና አጋጣሚ እንቅልፍ እየነሳ ይገኛል፡፡ ይህም ትግል ተጀመረ እንጂ ገና የመገባደጃ ደረጃ ላይ እንኳን አልደረሰም፡፡ ይህ ትግል እጅግ ፈታኝ እንደሚሆን ከጅምሩ እየታዘብን ነው፡፡ ያኔ ጥንት ባባቶቻችን ዘመን “ጠላትማ ምን ጊዜም ጠላት ነው ፤ አስቀድሞ መምታት አሾክሹዋኪውን ነው” ይባል እንደነበር ዛሬም ከዚያ ዘመን በባሰ ሁኔታ ወንድም ወንድሙን ለገንዘብ ሲል አሣልፎ እየሰጠ – ኤሣው ወንድሙን ያዕቆብን አንጀት ጠብ ለማትል እፍኝ ለማትሞላ ምሥር እንደለወጠው – በኛ የጉድ ዘመንም ለሞተ እንጀራ ሲባል የገዛ ወንድምን ለወያኔ መሸጥ እየተለመደ እንደሥነ ቃሉ ሀዘናችን ቅጥ ያጣበት ጊዜ ላይ ደርሰናል፡፡

የገደለው ባልሽ የሞተው ወንድምሽ፤
አዘንሽ ቅጥ አጣ ከቤትሽም አልወጣ።

ይህ በዘመነ ክርስቶስ በይሁዳ ጎልቶ የታዬ የሰዎች የክህደት ተግባር ዛሬም ተስፋፍቶና ግዘፍ ነስቶ መቀጠሉን በታጋይ ጎባው መልኬ ሰማዕትነት ልንገነዘብ ችለናል – በዚህ ብቻም የሚያቆም እንደማይሆን መገመት አይከብድም። ምክንያቱም የሆድ ነገር የዋዛ አይደለምና። ይህን ሰማዕት – ጎቤ መልኬን – የገደለም ያስገደለም ዋጋቸው አንድ ነው። “ደስ” የሚለው ደግሞ ገዳይም አስገዳይም እንደጎባው ሁሉ ጥርኝ አፈር ይሆናሉ። ልዩነቱ ጎባው አለመሞቱ ነው፤ እንደክርስቶስ በሦስተኛው ቀን ሥጋዊ ሞትን አሸንፎ አልተነሳም እንጂ የሞተ መስሎ ዘላለማዊ ሞትን ረትቷል – እኛም ቤተሰቡም በዚህ ልንደሰት እንጂ ልናዝን አይገባም። መሞት ማለት ለእዳሪ ለሚውል ትንሽ ነገር ኅሊናን ሸጦ በቁም መሞት ነው። እናም የገዳዮችና አስገዳዮች ሞት ዘላለማዊ መሆኑን የምገልጽላችሁ በጎባው ሞት በመንፈስ በመቅናትና በሰይጣናቱ ዕኩይ ተግባር ደግሞ ከልብ በማዘን ነው። ልብ ለሚል ይህ ክስተት ትልቅ አስተምህሮ አለው። የሰው ባሕርይ እንዲህም የገማና የከረፋ በመሆኑ ፍርዱን ከላይና ከታሪክ ከመጠበቅ ውጪ ለጊዜው ምንም ማድረግ አይቻልም – ቢያንስ እዚህ አዲስ አበባ ውስጥ ያለነው።
ብሎም ቢሆን የሕዝብ ትግል በየአቅጣጫው ቀጥሏል። የዚህን ጀግና መስዋዕትነት በመዘከር ወያኔን ሳይፈሩ ጎንደር ውስጥ ሰሞኑን ወጣቶች ስፖርት ሜዳ ውስጥ ያደረጉት ትግል ታሪክ የሚዘነጋው አይደለም።

በጎንደርና በጎጃም ሕዝቡ ዳሽን ቢራን ጨምሮ የወያኔ ድርጅቶችን ምርቶችና አገልግሎቶች ላለመጠቀም የወሰደው ቆራጥ እርምጃ ፍሬ ማፍራቱን እየሰማን ነው። ይህ ሕዝብ በርግጥም ከቆረጠ ያኮራል። ዳሽን ቢራ በየቡና ቤቱ መደርደሪያ ሲያሞቅ ይገኛል እንጂ ማንም እየጠጣው እንዳልሆነ ከሥፍራው የሚደርሱን መረጃዎች ይጠቁማሉ። ሰዎች ሲጠጡ ቢታዩ እንኳን ባካባቢው የሚገኝ ታዛቢ “ውይ ወንድማለም፣ የወንድሞችህን ደም ትጠጣለህ?” እያለ ያሳፍራቸዋል። በዚህ መልክም ቢራው እየከሰረ በዚያ አካባቢ ከሞላ ጎደል ከገበያ እየወጣ ነው። ይህ አኩሪ ድርጊት በሁሉም ሥፍራዎች መለመድ አለበት።

በዚህና በሌሎች ተዛማጅ እርምጃዎች የተነሣ የወያኔው ካዝና እየሳሳ መጥቶ ምናልባት ከጥቂት ጊዜ በኋላ ደሞዝ የሚከፍሉትም ሊያጡ እንደሚችሉ ትንበያዎች አሉ። ከጂቡቲ በኩል እንደምንሰማው ከሆነ ደግሞ ዕቃ ከውጭ ሀገራት መግባቱን አቁሟል ወይም ቢያንስ እጅግ ቀንሷል። ምክንያቱም ሀገሪቱ በቂ የውጭ ምንዛሬ የላትም። መድኃኒትንና የውኃ ማጣሪያ ኬሚካሎችን የመሳሰሉትን ጨምሮ ለመሠረታዊ ፍጆታዎች መግዣ የሚሆን እንኳን እያጣች በማስመሰል እንጂ በእውነት እየኖረች እንዳልሆነ የሚጠቁሙ ብዙ ፍንጮች ይታያሉ። ያለች እየመሰለች ግን ነፍሷ ሊወጣ በጣዕረ ሞት አፋፍ ላይ የምትገኝ አሳዛኝ ሀገር ነች – ሀገራችን ኢትዮጵያ። ለውጪ ታዛቢ በአስፋልታችንና በሕንጻዎቻችን ሳቢያ ያለን ሊመስለው ይችላል – ግን ውሸት ነው፤ የለንም። ይህች ታሪካዊ ሀገር ጳጉራም ውሻ ከሆነች ዋል አደር አለች – አለ ሲሉት እንደሚሞተው። አጭበርባሪና ሌባ፣ ማይም ዘራፊና ቀማኛ ብቻ እየገነነ ትሁትና የተማረው ጨዋ የማኅበረሰብ ክፍል እየኮሰመነና እየወደቀ የሚገኝባት ብቸኛዋ የዓለማችን መንደር ሆናለች – ኢትዮጵያ።

…. በዚህም አለ በዚያ የሚቀረው የከፈን ጨርቁን መግዛት እንጂ ወያኔ አለ ማለት የማይቻልበት ሁኔታ ተፈጥሯል። ግን የነጋበት ጅብ መጥፎ ነውና ወያኔ ሞተ ሲባል ይበልጥ ምናባዊ እንጂ እውናዊ አድርገን ባንወስደው የተሻለ ነው፤ አንድን ነገር ብዙ ማጋነን ያሳንፋልና ገና ብዙ መሥራት ይጠበቅብናል። በሌላም በኩል “የምትስቅ ሴትና የሚነቃነቅ እንጨት(ዛፍ)…” የሚለውን ነባር ብሂል መርሣት አይኖርብንም። እንዲሁ እየተንገዳገዱ ብዙ ዓመታትን ሊያስቆጥሩም ይችላሉና መተባበርና ልዩነቶችን በማስወገድ ለአንዲት ሀገር ምሥረታ መሰለፍ ያስፈልጋል። እንደ እስካሁኑ በረባ ባልረባው እየተመነቃቀሩና ጎራ በመለየት እየተፏከቱ በጅልነትና በማያዋጣ ብልጣብልጥነት መቀጠሉ የወያኔን ዕድሜ ከማራዘም በዘለለ የትም አያደርስም። በተለይ በሞቀ ቤት የሚኖሩ ሰዎች የምሥኪን ዜጎቻቸውን ችግር ተረድተው ከያዙት የግትርነት አቋም ካልተመለሱ መከራችን ሳያባራ ይቀጥላል። በተለይ ከመርዘኞቹ የጎሣ ፖለቲካና ከሃይማኖት ጽንፈኝነት ራስን ካላቀቡ ችግራችን ከአሁኑም እንደሚገዝፍና ሊቀለበስ ወደማይችል የመከራ አዙሪት ሊከተን እንደሚችል መረዳት ይገባል። በጎሣና በዘር፣ በሃይማኖትና በወንዝ ልጅነት መደራጀት ከወንጀልና ከኩነኔ ወይም ከኃጢአት መመደብ አለበት። የትም ሀገር አልሠራም – አይሠራምም። የቀጣፊዎች ከኑሮ ችግር ማምለጫ ዘዴ  ሲሆን ነው የታዘብነው፤ ብዙዎች የዋሃን ሲያልቁበት ነው ያየነው።

አንድ ኢኮኖሚ ከተንኮታኮተ ግለሰብም ይሁን መንግሥት ኃይሉ ይሟሸሻል፤ ጉልበቱ ይዝላል፤ ተሰሚነቱ እየቀነሰ ይሄዳል፤ የተፈሪነት ግርማ ሞገሱም እንደጤዛ ይረግፋል። ማዘዝ መናዘዝ የሚቻለው የኢኮኖሚ ክንድ ሲፈረጥም ነው። ወያኔ በአሁኑ ወቅት ሁሉንም ምናልባትም ብዙ ነገሩን አጥቶ ቆሌው የተገፈፈና በደመነፍስ የሚንጠራወዝ ግን ግን በኃያላኑ የምርኩዝ ድጋፍ ብቻ የሚኖር የአጋንንት ውላጅ ነው። ዕድሜ ለኦርቶዶክስና ለአማራ እነዚህ የሰው ሀዘን በደስታ የሚያሰክራቸው የውጭ ኃይላት ለታሪካዊ የበቀል ቁርሾኣቸው እርካታ ሲሉ ኢትዮጵያን በቀላሉ አይተዋትም፤ እናም ወያኔን እስከመጨረሻ ይፈልጉታል – እንደሚፈልጉትም ወያኔ ያውቃል – የክፉዎች መንፈስ አንድ ነውና ተመሳሳይ የጥፋት ዓላማ እርስ በርስ ይፈላለጋሉ፤ ለፕሮፓጋንዳ ፍጆታ ሲባል የሚነዛውን የዚያ ማዶና የዚህ ማዶ የወሬ ቋትና

ዲፕሎማሲያዊ የለዘበ ንግግር ተውት። ዞሮ ዞሮ የመጨረሻ ተስፋችን ግን ፈጣሪዋ የማይዘነጋት መሆኑ ነው። ከበቂ በላይ ተፈትናለችና በቶሎ ያስታውሳታል ብለን እናምናለን።

ገንዘብን በሚመለከት … እርግጥ ነው – ከሕዝቡ በተለያዩ ህገ ወጥና ህግ መሰል የጫካ ህጎች በመመራት ወያኔ ከሕዝብ እየዘረፈ ብዙ ብር ሊኖረው ይችላል። በመዝረፍ የታወቀ ቡድን ገንዘብ ቀርቶ ነፍስን ሲዘርፍ ቅር አይለውምና ይህን ግፋፎ ብር በማምረትም በመቀማትም ብዙ የስዕል ወረቀት(ብር) ሊያከማች ይችላል። ዋናው ግን የብሩ መብዛትና ማነስ አይደለም። የውጭ ምንዛሬ ነው ቁልፉ። ወንዝ የማያሻግር ብር ግፋ ቢል የጎጃምን ጤፍና የከፋን ቡና ያጋብስበት እንደሆነ እንጂ እንደቀድሞ የጦር ጀትና ታንክ የሚገዛበት ዶላር እንደልቡ ሊያገኝ አይችልም – ዲያስፖራዎችም በዚህ ረገድ – ማለትም ወያኔን ከዶላር በማራቁ በኩል – እያደረጉት ያሉት ነገር ሊዘነጋ አይገባውም፤ በርትተው ይቀጥሉበት – ጅምራቸው ፍሬ እያፈራ ነው። ወያኔን መታገል በሚያውቅበት በጦር መሣሪያ ብቻ ሣይሆን በማያውቅበት በዚህን መሰሉ የኢኮኖሚ ጦርነትም ጭምር አስጨንቆ በመያዝ ነው። ይህን እያየን ስለሆነ እንመሰክራለን። ወያኔዎች የማያውቁበት ጦርነት ውስጥ ገብተው እየዳከሩ ናቸው። መግደሉም፣ ማሰሩም፣ ደብዛን ማጥፋቱም፣ ማሰቃየቱም…. የሰለቻቸው ይመስላል – ግን ይሰለቻቸዋል ተብሎ ሊታመን በፍጹም አይገባም – ለአባባል ያህል ነው፤ እነሱ መግደልና ማሰቃየት የሚሰለቻቸው ሲጠፉ ብቻ ነው – አስተሳሰባቸውና አመለካከታቸው ሲጠፉ ለማለት ነው እንጂ በአካል ይጥፉ እያልኩ አይደለም። ሳስበው የአራት ኪሎን ቤተ መንግሥት “አጉራህ ጠናን” ሊሉ የተቃረቡ ይመስላል። ምኞት ሊመስል ይችላል። ወደ እውነት የተጠጋ ምኞት ነው ብዬ ብከራከር ደግሞ የሚያዋጣኝ ይመስለኛል – (በኔና በናንተ መካከል ይቅር እንጂ ደፋር ከመጥፋቱ በስተቀር ቤተ መንግሥቱ እኮ ባዶ ከሆነ ሰነበተ። የሚያስተዳድረን እኮ የጭቡ አምላክ ነው። በደመ ነፍስ እየተነዳን ይመሻል፤ ይነጋል። ህግ የለም፤ ፍትህ የለም፤ ባንዴራ የለም፤ የኔ ነው የምትለው የጋራ የሆነ ሀገራዊ ነገር የለም…።) … ለማንኛውም ፈጣሪ ኢትዮጵያን እንዲያስባት ሁላችን ከልብ እንጸልይ። እኛ ራሳችንም ከክፋትና ከተንኮል፣ ከቂመኝነትና ከበቀለኝነት እንራቅ። ነገር ሲያጥር ጥሩ ነውና ቻው።